https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No. 55
ADDIS ABABA 16th Auguast, 2018

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፬/፪ሺ፲ ዓ.ም
የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር
(ማሻሻያ) አዋጅ .....ገጽ ፲ሺ፬፻፷፮
ማረሚያ ቁጥር ፲፫/፪ሺ፲ .....ገጽ ፲ሺ፬፻፷፱

Content

Proclamation No.1094/2018
Addis Ababa City Government Revised Charter (amendment) Proclamation.……Page 10426
Corrigendum No.13/2010 …….. age 10429

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፬/፪ሺ፲

የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፪/፲፱፻፺፱ (እንደተሻሻለ) በአንቀጽ ፷፰ (፩) ላይ ጠቅላላ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ የሚፈጸም መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፰ ላይም ምርጫን አስመልክቶ በከተማ መስተዳደሩ የሚከናወኑ ምርጫዎች በሀገሪቱ የምርጫ ህግ መሠረት እንደሚከናወኑ የሚደነግግ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ምክር ቤት የስራ ዘመኑ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም የሚጠናቀቅ ሲሆን በድጋሚ ካልተመረጠ ወይም የሕግ ማሻሻያ ካልተደረገ በስተቀር ቀጣይ ሥራ ለመስራት ሥልጣን ስለማይኖረው ምርጫ እስከሚከናወን ድረስ ሥራውን እንዲቀጥል የሕግ ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ምርጫ ተከናውኖ ምክር ቤት እስከሚደራጅ ድረስ አሁን ያለው ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ስራውን ይዞ እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

Proclamation No. 1094/2018

A PROCLAMATION TO AMEND THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT REVISED CHARTER PROCLAMATION

WHEREAS, it is provided for under Article 28 (1) of the Electoral Law of Ethiopia Amendment Proclamation No. 532/2007 (as amended), general election to the House of Peoples' Repersentatives shall be conducted every five years;

WHEREAS, it is stipulated under Article 8 of Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003 (as amended), election for the Councils at all levels of the City Government shall be conducted in accordance with the election laws of the country;

WHEREAS, it is found important to amend the law, unless election is conducted the Council shall not have the power to discharge it's duties, as the term of Office of the Council expires on July 7 /2018;

WHEREAS, it is found important to retain the existing Council and the executive organs to discharge its duties until election is conducted;

በምክትል ከንቲባነት መስተዳደሩን ለመምራት ብቃት ያለውን ሰው ከምክር ቤቱ አባላት ወይም ከምክር ቤቱ ውጪ ለመሾም ዕድል የሚሰጥ ድንጋጌ ማካተት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፱(፪) እና አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፬/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፲፱፻፺፮ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ረ) እንደሚከተለው ተሻሽሎ በአዲስ ፊደል ተራ (ረ) ተተክቷል፤

"ረ) የከተማውን ከንቲባ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል፤"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደሚከለው ተሻሽሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፯) ተጨምሯል፦

"፩/ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም ግን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ገጥሞ በአምስት ዓመት መጠናቀቂያ ወቅት ምርጫ ማካሄድ ያልተቻለ እንደሆነ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የምርጫ ጊዜው ሊራዘም ይችላል። ምክር ቤቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይኖረዋል፤ መደበኛ ስብሰባው በየሁለት ወሩ ይሆናል።"

WHEREAS, it is found important to incorporate a provision which allows appointment of competent Deputy Mayor either from the members of the Council or none members of the Council;

NOW,THEREFORE, in accordance with Article 49(2) and 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Government Revised Charter (amendment) Proclamation No. 1094/2018".

2. <u>Amendments</u>

The Revised Addis Ababa City Government Charter Proclamation No. 361/2003 (as amended) is hereby re-amended as follows:

1/ Paragraph (f) of sub-article (2) of Article 14 of the Proclamation is amended and replaced by the following new paragraph (f):

"f) elect, from among its members, the City Mayor;"

2/ Sub-article (1) of Article 15 of the Proclamation is amended as follows and the following new sub-article (2) and (7) is added:

"1/ The term of Office of the Council shall be five years; provided, however that; due to force majeure if it is not possible to conduct election at the end of the five years term, the House of Peoples Representatives may extend the election period. The Council shall have regular and extraordinary meetings and the regular meetings shall be held every two months."

"፪/የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ጊዜ እንዲራዘም የወሰነ እንደሆነ ቀጣይ ምርጫ ተደርጎ በምርጫው መሠረት አዲስ አስተዳደር እስኪደራጅ ድረስ በሥራ ላይ ያለው ምክር ቤትና አጠቃላይ የከተማ አስተዳደሩ በነበረበት ይቀጥላል።"

"2/ Without Prejudice to sub-article (1) of this article, When the House of peoples' Representatives decides to extend of the election the City Council until the next election period, the existing City Council and the whole city Adminstaration Shall be remain active until rearangement is based on the new election.

"፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን የተራዘመ እንደሆነ፣ በሥራ ላይ የሚገኙ በሕግ የተቋቋሙ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት አካላት ምርጫ እስከሚካሄድ ድረስ ተግባርና ኃላፊነታቸውን መወጣት ይቀጥላሉ።"

"7/ When the term of Office of the Council is extended pursuant to sub-article (1) of this Article, the existing Addis Ababa City Government organs established by law shall continue to discharge their duties and responsibilities until election shall be held."

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደሚከለው ተሻሽሏል፦

3/ Sub-article (3) of Article 22 of the Proclamation is amended as follows:

"፫/ ምክትል ከንቲባው ከምክር ቤት አባላት ውስጥ ወይም ከምክር ቤት አባላት ውጪ የሚሾም ሆኖ የሥራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል። ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፤ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መደተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

"3/ The Deputy Mayor shall be appointed either from the members of the Council or non members of the Councel, the term of Office of the Mayor shall be that of the Council provided the he may be removed from his post, prior to the end of such term, uponresignation, Suspension from Office of or termination of his membership in the Council, details thereof shall be set out by the inernal regulation of the Council."

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ከሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፲

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ፕብሊክ

ፕሬዚዳንት

3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of its approval 7th day of July by House of Peoples' of Representatives.

Done at Addis Ababa, 16th of the August 2018.

MULATU TESHOME (Dr.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

https://t.me/ethiopianlegalbrief @AbrhamYohanes

ማረሚያ ቁጥር ፲፫/፪ሺ፲

የኢትዮጵያ ጂኦ-ስፓሻያል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲ሺ፫፱/፪ሺ፲ አንቀጽ ፲፪ (፩) "የኤጀንሲውን የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ..." የተባለው "የኤጀንሲውን የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል" ተብሎ ይነበብ።

Corrigendum No.13/2010

Article 12(1) of Ethiopian Geospatial Information Agency Re-Establish the Proclamation No. 1079/2018 Amharic version which read as "The Agency complete and accurate books of account…" is hereby corrected and shall be read as "The Agency shall keep complete and accurate books of account."

0915735560